# “የጠቅላይ ሚኒስቴር ሐይለማርያም ንግግርና እንደምታው”

ከጊዜው ደረሰ

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሐይለማርአም ደሳለኝ ከታላንት ወዲያ ፓርላማ ተገኝተው በሰጡት ሀተታ፣ ባልተለመደ ሁኔታ የስርአቱን ጠንካራነት ደግመው ደጋግመው አንስተዋል፡፣ለወትሮ የሚፎክሩት በኢኮኖሚ አደግን ተመጠቅን በዴሞክራሲም ተንበሸበሽን በማለት ነበር ። አሁን ታዲያ ለምን ስለስርአቱ ጥንካሬ መናገር ላይ አተኮሩ ብሎ መጠየቅና ሁኔታውን መተንተን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቀላሉ የሚረዳው ቢሆንም አንድ ሁለት ነገር ልሰንዝር፡ለመሆኑ ለምንድነው ደግመው ደጋግመው ስርአቱ ጠንካራ ነው የሚሉት?

የህወሀት/ኢህአዴግ ሰወችን ማረጋጋት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት። በኦሮሚያና በአማራ፣ በኮንሶና በአዲስአበባ ወዘተ ክልል የተነሳውን የህዝብ እምቢ ባይነት ተከትሎ በመላ ሀገሪቱ ፍርሀት እየተሰባበረ ስለመጣ ህዝቡም በያደባባዩ ሳይቀር ስርአቱን እያወገዘ ስለሆነና አንድ ለአምስት በተሰኘው አሰራር ይዘነዋል በማለት ሲያሰፈራሩት የኖሩት ሁሉ ፍርክስክሱ ስለወጣ የራሳቸውን ሰወች ማረጋጋት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት አይዟችሁ ጠንካራ ነን ልንፈራርስ አይደለም ለማለት ነው።

እውነታው ግን አባሎቻቸው በተለይም የደሁብ፣ የኦፒዲኦና የብአዴን አባላቶችን ደጋፊወች በቅርብ ሁኔታውን የሚያውቁት ስለሆኑ በዚህ አይነት ንግግር የማይደለሉ መሆኑ ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ብቻ ብዙ የስርአቱ ባለሟሎች ሀገር ጥለው ሄደው በአሜሪካ ፣ በአውሮፓ፣ ካናዳና አውስትራሊያ ጥገኝነት እየጠየቁ ነው። አንዳንዶቹ ለጊዜው ጥገኛነት መጠየቃቸው ሁሉ ወሬው እንኳ እንዲሰማ አይፈልጉም፡ በአገኙት አጋጣሚ ቤተሰባቸውን ሁሉ ይዘው ነው እየፈረጠጡ ያሉት። ይህም በመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይፍጨርጨሩ እንጂ የደጋፊወቻቸውንና የባለስልጣናቱን ስደት እንኳን ሊያስቆሙት ሊያቀዘቅዙትም አይችሉም ። ሁሉም ለህይወቱና ቤተሰቡ ስለሚጓጓ ካሁኑ ነገሩ ሙሉ ለሙሉ ሳይጨልም ጥለው መውጣታቸው በተለይም በመካከለኛና ዝቅተኛ ቦታ ላሉ ባለስልጣኖች ሁሉ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ከመንጌና ከኢሰፓ ደጋፊወች ህዝብ ብዙ ተምሯልና።የስርአቱ ባለስልጣኖች በመጨረሻዋ ደቂቃ አውሮፕላን አስነስተው መብረር እንደሚችሉ ወይም አንዱ ኤምባሲ ገብተው ራሳቸውን እንደሚያድኑ ምንም ጥያቄ የለውም። ታዲያ በዚያች ሰአት ተራው ደጋፊ ምን ይውጠዋል? ጠቅላይ ሚኒስቴሩ በውነት የተረጋጋና ጠንካራ መንግስት የሚመሩ ከሆነ ለምንድነው ሴት ልጃቸው አሁንም ውጭ ሀገር የምትኖረው? ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ለመሆኑ አርከበ ለምንድነው ፓስፖርቱን የተነጠቀው፣ ሌሎችስ ? እንደኔ ግምገማ የሚችል በቦሌ ሌላው በባሌ እየሾለከ መኮብለሉ ይጠናከራል እንጂ አይቀንስም።

ህዝብን በማስፈራራት፡ትግሉን ማቀዝቀዝ ስለተፈለገ። ሌላው በዚህ ንግግራቸው ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያነሱት የርሳቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኒውዮርክ ሄደው ፈረንጆቹ ሁሉ “የእናንተ መንግስት ጠንካራ እንደሆነ ተረዳን እያሉ እሞገሱን” የሚለው ነው። ይህ አነጋገር ለፈረንጆቹ ታስቦ ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን ማስፈራሪያነት የተጠቀሙበት ንግግር ነው። ዋናው መልእክት ወደዳችሁም ጠላችሁም እንኳን እናንተ ፈረንጅ ሳይቀር ጠንካራነታችንን አምኖበታል፡ስለዚህም ምንም ልታደርጉን አትችሉም እናም ትግሉን ተውት ለማለት ነው።

እውነቱን ለመናገር ፈረንጆቹ ህወሀት/ኢህአዴግን እርግፍ አድርገው ባይወረውሩትም በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየረቋቸው፣ ግስጻውም እየተጠናከረ ነው፡ በቅርቡ ያሜሪካ ውጭ ጉዳይ ባለስልጣን፣ የካናዳ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የጀርመኗ ቻንስለር አዲስ አባባ ላይ የሰጡትን መግለጫ ማዳመጥ በቂ መረጃ ይሰጣል።

ያም ሆነ ይህ ጥያቄው እውነት ጠንካራ ከሆናችሁ ለምን የፈረንጅ ምስክር አሰፈለጋችሁ የሚል ነው? 99% ህዝብ የጠላው መንግስት ጠንካራ ነን ቢል ባየር ላይ የተንሳፈፈ መሰረት የሌለው ከህዝብ የተነጠለ መንግስት እንዴት ነው ጠንካራ የሚባለው?ጥንካሬው ከምን የመጣ ነው። እና እኛ ኢትዮጵያውያን በየቀኑ ስለምንኖርበት ሁኔታ መመስከር አንችልም እንዴ የሚለው ነው። ህወሀት/ኢህአዴግ ከላይ እንደጠቀስኩት በህዝቡ መጠላቱ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ

ከዛሬ ነገ ሆ ብሎ ተነስቶ ሊበላው እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለውም:: ራሱም ያውቀዋል። ዶክተር መረራ ነጻነት የራበው ህዝብ መሪወቹን ይባላል ይሉ ነበር። ስለዚህ ለመረዳት ከተፈለገ በቢሸፍቱ ባኢሬቻ በአል ላይ ፣ በጎንደርና ባህርዳር የሆነውን ማየት ነው።

እውነታው የሚያሳው ሕዝብ ሰብሰብ ባለበት ቦታ ሁሉ ህወሀት/ኢህአዴግ ይወገዛል። የሚይዝ የሚጨብጠው ጠፍቶበታል።በዚህም የተነሳ መንግስት ጉልበቱ ዝሏል። በግልጥ የሚታየው ሀቅ ትግሉ መልኩን እየቀየረ የቀጠለ መሆኑ ነው። ለምሳሌ በጎንደርና በጎጃም ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ንግግር ከማረጋቸው በፊት ሁለት ተከታታይ ቀኖች እንዲሁም ንግግር ባደረጉ ቀን ባልታወቁ ሰወች ቦንብ መወርወሩን ራሱ የመንግስት ሬዲዮና ቲቪ አምናል።

አዎ የመንግስት ወታደራዊ ጥንካሬው ከተቃዋሚው ከፍተኛ ነው። ሆኖም በህዝብ ድጋፍ አንጻር እዚህ ግባ የመንግስት ድጋፍ ባዶ ነው። ለዚህም ነው በየእለቱ የተቃዋሚው እንቅስቃሴ ስር እየሰደደ መንግስትና ሰራዊቱ እንደ ባእድ ሀይል እየታየ በማሽቆልቆል ላይ ያለው።ለዚህ ነው እስካሁን በጎንደርና በጎጃም ተከታታይ ወታደራዊ ዘመቻ ቢደረግም ተቃውሞውን መደምሰስ ያልተቻለው። ለዚህ ነው ወታደራዊ እዝ ቢመሰረትም እስካሁን ባኦሮሚያ ይህ ነው የሚባል የጸጥታ መሻሻል ያልታየው። እንዲያውም እንደሚነገረው የመንግስትን ወታደር በየሄደበት ቦታ ሁሉ ውጊያ የሚገጥመው ከህዝብ ጋር ነው።

ታዲያ ራስን ማሞኘት ካልሆነ በስተቀር በቦንብ እየጋየ የሚገኝ ሀገር ውስጥ በየቦታው ከህዝብ ጋር ጦርነት ውስጥ የሚገኝ ስርአት ጠንካራ ስርአት ነው ማለት ይቻላል ?ይህ ነው እውነታው። ለዚህ ነው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ንግግር ኢላማውን እንደሳተ ተኩስ ሊቆጠር የሚችለው። የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ንግግር ኢትዮጵያውያንን ከማስፈራራት ይልቅ ህዝቡ ስርአቱን ይበልጥ እንዲታዘበው የሚያደርገበት እድል ሰፊ ነው።

የኢንቨስተሮችና ቱሪስቶችን ፍርጠጣ ለመግታት። ሌላው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ መልእክት ለውጭ ኢንቨስተሮችና ቱሪስቶች ነው። የህዝብ መነሳሳቱና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቱሪስቶችም ኢንቨስተሮችም እንዲርቁ ስላደረገ ሰሞኑን ደግሞ በጎንደርና ጎጃም ቦንብ ስለፈነዳ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሙከራ ሀገር ሰላም ነው አትደናገጡ ለማለት ነው። ችግሩ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ መግለጫ በተሰጡ ቀን የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የአውስትራሊኢ የካናዳ ወዘተ መንግስታት ቀደም ሲል ለዜጎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እንዳይሄዱ ከሄዱም እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚያሳስበውን ማስጠንቀቂያ እንደገና ስላደሱት የኢትዮጵያ መንግስት ሰላም ነው ቢል ባይል ቱሪስቱም ኢንቨስተሩም ደፍሮ ለመምጣት እንደሚከብደው ነው። በዚህ አኳያም የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ንግግር በውጭ ዜጎች አኳያ በትዝብት የሚታይና ታማኒነት የጎደለው እንጂ ውጤታማ ሊሆን የማይችል ነው።

ከተናገሩት ይልቅ ያልተናገሩት ብዙ ያሳብቅባቸዋል

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከተናገሩት ይልቅ ያልተናገሩትን መመመልከት ደግሞ እጅግ ብዙ ጉዳይ እንድንገነዘብ ይረዳናል። ሐይለማርያም ደሳለኝ በሁለት ቀን ገለጻቸው ያሰወገዱት አንዱ ነገር በዴሞክራሲ ተንበሽብሸናል ሲሉ ራሳቸውን ያሞካሹበት የነበረውን ሀረግ ነው። በዚህ የሁለት ቀን ንግግራቸው እንደቀድሞው ጊዜ የዴሞክራሲ አባወራ ነኝ ለማለት ቀርቶ ቃሉን ለመንሳት እንኳ ሲተናነቃቸው ተደምጠዋል። ይህ ሁኔታ ስለስርአቱ ኪሳራ እጅግ ጥልቅ እንደሆነ ገላጭ ነው። ባጭሩ በስልጣን የቆዩት በጉልበተኛነት እንጂ በህዝብ ይሁንታ እንዳልሆነ ማመናቸውን ያመለክታል።ወዳጆቻቸው የነበሩት የውጭ መንግስታት ሳይቀሩም ደግመው ደጋግመው የሚየነሱት አንዱ ጉዳይ ይሕ ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ የምንፈልገው ዴሞክራሲያዊ መንግስትና ዴሞክርሲያዊ ስርአትን በመሆኑ፣ ሕወሀት/ኢህአዴግም የመምራት ብቃቱም ሆነ የህዝብ አመኔታ እንደሌለው በድጋሚ ስለተረጋገጠ ለስርአት ለውጥ መንገዱን ቢያመቻችና የለውጡ ተጠቃሚ ለመሆን ቢሞክር የተሻለ ይሆናል እላለሁ ።

ጊዜው ደረሰ